በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/ሬ፶/18

ቀን 28/05/2018 ዓ/ም

**ለአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ**

ባህርዳር

**ጉዳዩ፡-** ***የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል***

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/2017 አንቀጽ 16(4) በተደነገገው መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ቢሮዎችሁም በአዋጁ መሰረት በቁጥር ሲ.ሰቢ./07/81118 በቀን 20/04/18 ዓ/ም በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ የላካችሁልን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሰረት ተመልክተን በአዲስ **መመሪያ ቁጥር 37/2018 ዓ/ም** በሚል ሰጥተን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሙሉጎጃም እንየው

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትህ ቢሮ

## <u>መመሪያ ቁጥር 37/2018 ዓ.ም</u>

## <u>በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት</u>

## <u>የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ የተሻሻለው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር መመሪያ</u>

የአገራችን የጤና ፖሊሲ መከላከልን መሰረት አድርጎ የተቀረፀ በመሆኑ በመተግበር ላይ የሚገኘው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በሽታን በመከላከልና ጤናን በማበልፀግ የህብረተሰቡን የጤና ባለቤትነት በማረጋገጥ እና ዋና ዋና የጤና ችግሮችን በመፍታት ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት በማስፈለጉ፤

ፕሮግራሙን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ባለፉት አመታት ህብረተሰቡን በስራና በመኖሪያ አካባቢው በመገኘት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ ቤተሰብን ሞዴል ማድረግ የተቻለና በሁለተኛው የጤናው ሴክተር የለውጥ እቅድ ከተቀረፁት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች አንዱ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን በመሆኑቀበሌዎችንና ወረዳን ሞዴልለማድረግ ዋና የእቅዱ አካል እንዲሆን በመደረጉ፤

የህብረተሰቡን ባህል እና ወግ የሚያውቁ ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ባሉበት ቀበሌ ወይም አጎራባች ቀበሌዎች ወይም ወረዳ ውስጥ ተመልምለው  አስፈላጊውን ስልጠና ካገኙ በኋላ በተመለመሉበት አካባቢ የሚመደቡ በመሆኑ፤

ከአሁን በፊት በነበረው አሰራር አዳዲስ ባለሙያዎች ተመርቀው ሲመጡ በቅርብ ቀበሌ መመደብ፣ ክፍት ቀበሌ ሲገኝ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ማዛወር፣ ስርነቀል ዝውውር መስራት፣ ባለ ትዳር ለሆኑትም አብረው እያሉ የትዳር ነጥብ መስጠት፣ ወቅቱን የጠበቀ ዝውውር አለመስራት፣የተሿሚ ሚስት በሚል ጤና ኬላዎችን ባዶ በማድረግ ወደ ከተማ አካባቢ ባለ ጤና ኬላዎች እየደራረቡ መመደብ፣

ጤና ኤክስቴንሽን የሌለው ቀበሌና አንድ ጤና ኤክስቴንሽን ያለው እያለ ከተማ ዳር ላይ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ማጠራቀም የሚሉት ችግሮች ይፈፀም ስለነበር በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በቀረበ ቅሬታ መሰረት እና በሌሎች ሴክተሮች በቀበሌ ደረጃ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጤና ጥበቃ ቢሮው ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ጋር በመተባበር በ2002 ዓ/ም የጤና ኤክሽቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር፣ የመልቀቂያና ልዩ ልዩ የዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

ቢያወጣም በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከዞን ጤና ጥበቃ መምሪያና ከወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከራሳቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሚቀርብ ቅሬታ ይህ መመሪያ ለአፈፃፀም የሚያስቸግር እና አንዳንድ መመዘኛዎች አሁን ካለው የቢኤስሲ አሰራር/አስተሳሰብ ጋር የሚጣረስ በመሆኑ፤

የተገኘውን ውጤት በጥራት ለማስቀጠል በስራ ቦታቸው ተረጋግተው የሚሰሩ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስለሚያስፈልግ የወጣውን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሰው ኃይል ስምሪት መመሪያ አሻሽሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የአብክመ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ በአብክመ የተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 253 /2010 ዓ.ም በአንቀጽ 96 ንዑስ ቁጥር 2 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡



# መመሪያ ቁጥር 37/2018 ዓ.ም

# በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

# የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ የተሸሻለው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር መመሪያ

የአገራችን የጤና ፖሊሲ መከላከልን መሰረት አድርጎ የተቀረፀ በመሆኑ በመተግበር ላይ የሚገኘው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በሽታን በመከላከልና ጤናን በማበልፀግ የህብረተሰቡን የጤና ባለቤትነት በማረጋገጥ እና ዋና ዋና የጤና ችግሮችን በመፍታት ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት በማስፈለጉ፤

ፕሮግራሙን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ባለፉት አመታት ህብረተሰቡን በስራና በመኖሪያ አካባቢው በመገኘት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ ቤተሰብን ሞዴል ማድረግ የተቻለና በሁለተኛው የጤናው ሴክተር የለውጥ እቅድ ከተቀረፁት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎች አንዱ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን በመሆኑ ቀበሌዎችንና ወረዳን ሞዴልለማድረግ ዋና የእቅዱ አካል እንዲሆን በመደረጉ፤

የህብረተሰቡን ባህል እና ወግ የሚያውቁ ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ባሉበት ቀበሌ ወይም አጎራባች ቀበሌዎች ወይም ወረዳ ውስጥ ተመልምለው አስፈላጊዊውን ስልጠና ካገኙ በኋላ በተመለመሉበት አካባቢ የሚመደቡ በመሆኑ፤

ከአሁን በፊት በነበረው አሰራር አዳዲስ ባለሙያዎች ተመርቀው ሲመጡ በቅርብ ቀበሌ መመደብ፣ ክፍት ቀበሌ ሲገኝ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ማዛወር፣ ስር-ነቀል ዝውውር መስራት፣ ባለ ትዳር ለሆኑትም አብረው እያሉ የትዳር ነጥብ መስጠት፣ ወቅቱን የጠበቀ ዝውውር አለመሰራት፣የተሿሚ ሚስት በሚል ጤና ኬላዎችን ባዶ በማድረግ ወደ ከተማ አካባቢ ባለ ጤና ኬላዎች እየደራረቡ መመደብ፣

ጤና ኤክስቴንሽን የሌለው ቀበሌና አንድ ጤና ኤክስቴንሽን ያለው እያለ ከተማ ዳር ላይ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ማጠራቀም የሚሉት ችግሮች ይፈፀም ስለነበር በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በቀረበ ቅሬታ መሰረት እና በሌሎች ሴክተሮች በቀበሌ ደረጃ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጤና ጥበቃ ቢሮው ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ጋር በመተባበር በ2002 ዓ/ም የጤና ኤክሽቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር፣ የመልቀቂያና ልዩ ልዩ የዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

ቢያወጣም በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የመስክ ጉብኝቶች፣ ከዞን ጤና ጥበቃ መምሪያና ከወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከራሳቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሚቀርብ ቅሬታ ይህ መመሪያ ለአፈፃፀም የሚያስቸግር እና አንዳንድ መመዘኛዎች አሁን ካለው የቢ.ኤስ.ሲ. አሰራር/አስተሳሰብ ጋር የማጣረስ በመሆኑ፣

የተገኘውን ውጤት በጥራት ለማስቀጠል በስራ ቦታቸው ተረጋግተው የሚሰሩ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስለሚያስፈልግ የወጣውን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሰው ኃይል ስምሪት መመሪያ አሻሽሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የአብክመ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ በአብክመ የተሸሻለው የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 253 /2010 ዓ.ም በአንቀጽ 96 ንዑስ ቁጥር 2 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የተሻሻለው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 37/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ **"የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች"** ማለት እውቅና ካለው የጤና ተቋም በሰርቲፊኬት፣ በደረጃ 3 እና በደረጃ 4 የትምህርት ደረጃ ተመርቀው በከተማም ሆነ በገጠር ቀበሌ ተመድበው በጤና ኤክስቴንሽን ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ነው፤

2/ **"የስራ ልምድ"** ማለት በመንግስት መ/ቤቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ህጋዊ አቋምና የተሟላ የውስጥ አደረጃጀት ባላቸው የግል ድርጅቶች ውስጥ በማንኛውም የስራ አይነት በቋሚነት ወይም በኮንትራት የወር ደመወዝ እየተከፈላቸው በመደበኛ የስራ ሰዓት የመንግስት ግብር እየተከፈለ የተሰራ የስራ ልምድ ማለት ነው፡፡ ሆኖም ከጤና ሙያ ውጭ የተሰራ የስራ ልምድ የሚያገለግለው ለዝውውር ብቻ ነው፤

3/ **"ምደባ"** ማለት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ከተመረቀች በኋላ ስራተኛዋ ካላት ሙያና ደረጃ አኳያ ታይቶ አገልግሎት የምትሠጥበትን ቦታ ማሳወቅ ወይም መደልደል ነው፤

4/ **"ዝውውር"** ማለት አንድ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ከምትሰራበት ቀበሌ ወይም ወረዳ ወይም ዞን ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ወረዳ ወይም ዞን አዛውሮ ማሰራት ነው፤

5/ **"የጋብቻ ማስረጃ"** ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ወይም በሃይማኖት ተቋም ወይም በባህላዊ ጋብቻ /የአገር ሽማግሌ/የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

6/ **"የህክምና ቦርድ ማስረጃ"** ማለት በመንግስት ሪፈራል ሆስፒታል ደረጃ በሀኪሞች ሜዲካል ቦርድ ታማሚው ያለበትን የጤና ሁኔታና ምን አገልግሎት/ሊ.ታገዝ እንደሚገባ የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ ነው፤

7/ **"የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ"** ማለት በአየር ጠባይ ተስማሚ አለመሆን ወይም በመሠረተ ልማት ኋላ ቀርነት የሚታይበት፣ ከወረዳው ርዕሰ ከተማ ያለው ርቀትና በሌሎችም መስፈርቶች የተሰጠ የቦታ ደረጃ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት

1/ የተጀመረው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዘላቂና በህብረተሰቡ ጤና ላይ መሠረታዊና ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዲችል ለማድረግ፤

2/ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከቦታ ወደ ቦታ ተዛውሮ የመስራት መብትን ለማረጋገጥና ሥራን ማዕከል ያደረገ ስምሪት ለመስጠት

3/ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች የመከላከሉን ተግባር የተሳለጠ ለማድረግ እንዲችሉ ለማነሳሳት፣ ታታሪና ብቃት ያላቸውን የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሙያው እንዲቆዩ ለማድረግ፤

4/ መከላከልን መሠረት ያደረገውን የጤና ኤክስቴንሽን ተግባር በዘላቂነት ለማስቀጠል፤

5/ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ኬርየር እና የትምህርት ደረጃም እያደገ በመምጣቱ የመመሪያውን መሻሻልአስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

በክልሉ በሚሠሩ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ዝውውር አፈፃፀም

## 5. ዝውውር ከመፈፀሙ በፊት መረጋገጥ ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ ዝውውር የሚፈፀመው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ባልተመደበባቸው ወይም ተለቀው ክፍት በሆኑ ቀበሌዎች ብቻ ይሆናል፤

2/ በቋሚነት በተመደቡበት ቀበሌ ቢያንስ 2 አመት ያገለገለች፤

3/ በተቀመጠው የአተገባበር መመሪያ መሰረት ቢያንስ ለአንድ ሺህ አባወራ/እማወራ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ማስፈለጉ ሲረጋገጥ (ለአንድ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ 333 አባወራ ወይም እማወራ) በሚለው ተጨማሪ የሰው ኃይል ማስፈለጉን በማረጋገጥ፤

4/ ከተማ ቀበሌዎች ላይ የሚመደቡ ወይም የሚዛወሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያወች በደረጃ አራት ደረጃቸውን ያሸሻሉ ወይም የተመረቁ ሲ. ኦ ሲ. ያላቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ፣

5/ የዝውውር ማስታወቂያ ለሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በሚያመች መንገድ እንዲለጠፍ/እንዲደርስ እና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችም ዝውውር መጠየቂያ ፎርሙን በመሙላት በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የሚፈልጉትን ቀበሌ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ በመዘርዘር በተዘጋጀው የዝውውር መጠየቂያ ፎርም ሞልተው በክላስተር ጤና ጣቢያው በኩል እንዲያቀርቡ ሲደረግ፤

3/ ለቀበሌዎች የተሰጠውን ደረጃ ሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዲያውቁት እና በተመደቡበት ቀበሌ በመስራታቸው የሚሰጣቸው ነጥብ ስንት እንደሆነ በቅድሚያ ማወቃቸውን በማረጋገጥ፤

4/ ዝውውሩን በአግባቡ ለመፈፀም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሞሉት ቅጽ በጥንቃቄ ተሞልቶ በወቅቱ ዝውውሩ በሚፈጸምበት ደረጃ በጤና ጣቢያ፣ በወረዳ ሲቪል ሰርቪስ እና ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፣ ዞን ሲቪል ሰርቪስና ጤና ጥበቃ መምሪያ እና ጤና ጥበቃ ቢሮ መድረሱ ሲረጋገጥ፤

5/ ህጋዊ ጋብቻ ማስራጃ ያላቸው ባለሙያዎች ዝዉዉር ከመስራቱ በፊት 6ወር ከግል ማህደራቸው መያያዝ አለበት።

## 6. የዝውውር ማወዳደሪያ መስፈርቶች

1/ ዝውውሩ ከመታየቱ በፊት ባሉት ሁለት የመጨረሻ የዕቅድ አፈፃፀም መገምገሚያ ወቅት የተሞላ የስራ አፈጻጸም ውጤት 40 % (የተገኘው ውጤት በ0.4 እየተባዛ ይያዛል ለአብነት በስራ አፈጻጸም ውጤት በጣም ከፍተኛ ሆኖ ውጤቱ 88 ቢሆን 88 ሲባዛ በ0.4 = 35.2 ይሆናል፡፡)

2/ የስራ ልምድ ከ20 % የሚያዝ ሆኖ 13 ዓመት እና በላይ አገልግሎት ያላት ከሆነ 20 ነጥብ የምታገኝ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከ13 ዓመት በታች አገልግሎት ያላት ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ተወዳዳሪ ሆና ስትቀርብ በዚሁ ስሌት ውጤቱ ተሰልቶ ይሰጣታል፡፡ (ለምሳሌ 12 ዓመት ያገለገለች 12 ሲባዛ በ20 ሲካፈል ለ13 = 18.46 ይሆናል ማለት ነው)፡፡

3/ ለትዳር የሚሰጥ ነጥብ 5 %፤

4/ የማህደር ጥራት 5 % የሚይዝ ሆኖ አፈፃፀሙ ሐምሌ 2010 ዓ.ም በተሻሻለው የመንግስት ሠራተኞች ምልምለና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 4.5.2 መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

5/ የቀበሌዎች ለኑሮ ተስማሚነት ደረጃ 30% የሚይዝ ሆኖ ቀበሌዎችን በ3 ምድብ ወይም ደረጃ በመክፈል ማለትም በከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ፣ በመካከለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ በሚል በየሦስት አመት የወረዳው ሲቪል ሰርቪስ እና የጤና ጽ/ቤት በጋራ የገጠር መሰረተ ልማት መስፋፋት እና የአየር ንብረት ሁኔታ አስቸጋሪነት ቀበሌው ከወረዳው ርዕሰ ከተማ ያለው ርቀት ግምት ውስጥ በማስገባት ደረጃ በማዘጋጀት ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በማቅረብ ደረጃው እየተወሰነ ከዚህ በታች በተመላከተው ደረጃ ነጥብ ይሰጣል፡፡"

ሀ) በከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 30%

ለ) በመካከለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 25%

ሐ) በዝቅተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ናቸው ተብለው ለተፈረጁ ቀበሌዎች 20%

## 7. ዝውውሩ የሚፈፀምባቸው ደረጃዎች

1/ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ፤

2/ ከወረዳ ወደ ወረዳ፤

3/ ከዞን ወደ ዞን፡፡

## 8. የዝውውር ዓይነቶች

1/ መደበኛ ዝውውር

ሀ) አዲስ ምሩቃን ወደ ጤና ተቋም ከመቀላቀላቸው በፊት ነባር የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በውድድር ከነበሩበት ቀበሌ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፣ ዞን ወደ ሌላ ቀበሌ፣ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፣ ዞን ተዘዋውረው እንዲሰሩ የሚደረግበት ሁኔታ ሲሆን ዝውውሩም በሚከተለው መንገድ እንዲፈጸም ይደረጋል፤

ለ) ደረጃ 4 የሆኑ የደረጃ 4 የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው በገጠር የሚሰሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የማወዳደሪያ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በዚህ መመሪያ እየተወዳድሩ ወደ ከተማ ቀበሌዎች መግባትና የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ሆነው መዘዋወር ይችላሉ፤

ሐ) ደረጃ 3 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር ይስተናገዳሉ፤

መ) ዝውውር ጠያቂ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በሚሰሩበት ቦታ ሁለት አመትናከዚያ በላይ ያገለገሉ ከሆኑ በወቅቱ ሞልተው በሚልኩት የዝውውር ፎርም መሠረት ይወዳደራል፡፡

ሠ) ከዞን ዞን የተዛወሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በተዛወሩበት ዞን ውስጥ ክፍት ቦታዎች ካሉ በዚያዉ ዞን ዉስጥ ዝዉዉር ከሞሉ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ጋር እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው ሲሆን ተወዳድረው በተመደቡበት ቦታ የመስማራት ግዴታ አለባቸው፤

ረ) ህጋዊ የጋብቻ ማስረጃ የሚያቀርቡ ባለትዳሮች ዝውውር የሚጠይቁት አንድ ላይ ለመኖር ወይም ለመቀራረብ ሲሉ ይሆናል፡፡ የጋብቻ ማስረጃው ተቀባይነት ሲያገኝ ለትዳር 5 ነጥብ ይሰጣል፤

ሰ) ንድ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ የዝውውር ጥያቄ ፎርም ስትሞላ የጋብቻ ማስረጃ በስራተኞዋ የግል ማህደር ላይ ከሰድስት ወርናበፊት የተያያዘ መሆን አለበት፤

ሸ) የትዳር አጋሯ የመንግስት ሰራተኛ ቢሆኑም ባይሆኑም የጋብቻ ማስረጃው ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (ረ) መሰረት ይተያያዘና የመንግስት

ሰራተኛ ከሆኑ ከሚሰሩበት መ/ቤት የመንግስት ሰራተኛ ካልሆኑ ደግሞ ከሚኖሩበት ቀበሌ የኗሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ወደ አወዳዳሪው ተቋም መላክ አለበት፤

ቀ) ባለሙያዋ ለመዛወር ስትጠይቅ የባልና ሚስት አገልግሎት ተደምሮ ሲካፈል በሚኖረው አማካይ የአገልግሎት ዘመን ተይዞ እንድትወዳደር ይደረጋል፤ ሆኖም የራሷ የአገልግሎት ዘመን ከአማካይ ውጤቱ የተሻለ ከሆነ በቀጥታ ይያዝላታል፤

በ) ባለሙያዋ በዝውውር መጠየቂያ ቅጽ ላይ መረጃውን በትክክል መሙላት ይጠበቅባታል። ሳይሞሉ ቀርተው ዝውውሩ በተናጠል ከታየ በኋላ የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም።

2/ በማህበራዊ እና በጤና ችግር ምክንያት የሚፈፀም ዝውውር፣

ሀ) የጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች ከሚሠሩበት ቦታ የጤና መታወክ ችግር ሲያጋጥማቸውና ባሉበት ቦታ የህክምና አገልግሎት ማግኘትና መስራት እንደማይችሉ ሪፈራል ሆስፒታሎች በሐኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ ህክምና ሊያገኙ በሚችሉበት የጤና ተቋም አቅራቢያ ባለው ክፍት የስራ ቦታ ያለ ውድድር የቆይታ ጊዜውን ሳይጠብቁ ዝውውሩ ይፈቀድላቸዋል። ሆኖም የጤና ችግራቸው እስካልተፈታ ጊዜ ድረስ የህክምና ቦርድ ማስረጃው እስከታደሰ ድረስ ይጠቀሙበታል፤

ለ) በቤተሰብ ችግር ምክንያት ወይም የህግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው ሆነው ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ባለሙያዎች የመደበኛ ዝውውር ጊዜውን ሳይጠብቅ ሲሰሩበት በነበረው ተመሳሳይ ክፍት የስራ ቦታ ከተገኘ እንዲዛወሩ ይደረጋል።

3/ የእርስ በርስ ዝውውር

ሀ) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (ሀ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች የእርስ በእርስ ዝውውር ማድረግ ከፈለጉ የመደበኛውን የዝውውር ጊዜ ሳይጠብቅ ዝውውሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፤

ለ) የዝውውሩ ሁኔታ ከወረዳ ወደ ወረዳ ወይም ከዞን ወደ ሌላ ዞን ከሆነ በሁለቱ ወረዳዎች ወይም ዞኖች እውቅናና ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፤

ሐ) የእርስ በእርስ ዝውውር በሚካሄድበት ወቅት ተዘዋዋሪዎች ተመሳሳይ ደረጃ እና ደመወዝ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ ሆኖም ደረጃቸው ተመሳሳይ ሆኖ የአንድ ደረጃ ወይም 3 እርከን የደመወዝ ልዩነት ቢኖርም ላኪና ተቀባይ መ/ቤቶች ከተስማሙ ዝውውሩን ማከናወን ይቻላል፡፡

4/ ከቀበሌ ወደ ሌሎች የጤና ተቋማት የሚደረግ ዝውውር፣

ሀ) ከቀበሌ ወደ ጤና ጣቢያ እና ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ባሉ ክፍት የስራ መደቦች ዝቅተኛውን ተፈላጊ ችሎታ እስካሟሉ ድረስ በሌሎች ጤና ባለሙያዎች የዝውውር እና የደረጃ እድገት የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

ለ) ከወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ እና ከዞን ወደ ሌላ ዞን ለሚካሄድ ዝውውር በመደበኛው የጤና ባለሙያዎች የዝውውር አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ፎርም እየሞሉ የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ምደባና የተቋማት ኃላፊነት

### 9. ምደባ

1/ የአዲስ ምሩቃን የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ምደባ ከመከናወኑ በፊት የነባር ሰራተኞች ዝውውር መጠናቀቅ ይኖርበታል፤

2/ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመደበኛው ዝውውር ከመሰራቱ በፊት በሙያ ማሻሻያም ይሁን በመደበኛ ስልጠና የተመረቁ ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከመጡ በጊዜያዊነት መድቦ በማሰራት የመደበኛው ዝውውር በሚሰራበት ጊዜ በማወዳደሪያ መስፍርቶች መሰረት በሚመጥናቸው ቀበሌ ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤

3/ ነባር የጤና ኤስቴንሽን ባለሙያዎች ትምህርታቸዉን አሻሽለው ሲመለሱ ምደባ የሚሰጣቸው በጊዜያዊነት ሆኖ የሚመደቡትም አገልግሎታቸውን መሰረት በማድረግ ይሆናል፤

4/ በአዲስ ተመርቀው የሚመጡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ምደባ በጊዜያዊነት ሆኖ የሚመደቡትም በእጣ ይሆናል፡፡

## 10. የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት፣

1/ የጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የመደበኛ ዝውውር በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ ተግባራዊ እንዲሆን የውድድር መስፈርቱን መሰረት በማድረግ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት አስተዳደር ቡድን ቴክኒካል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡ ችግሮች ሲያጋጥሙም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

ለ) በዞኖች የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የተሰራውን ስምሪት ይከታተላል፤

ሐ) ከዞኖች የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የሚመጣውን መረጃ መረጃ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ በሚገኘው ውጤት መሰረት አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡ በወቅቱ የተሰራውን ዝውውር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፤

መ) በክልል ደረጃ የሚያስፈልገውን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ዕቅድ ያዘጋጃል ፤የተፈቀዱ መደቦች በሰው ሃይል መሟላታቸውን ይከታተላል ፤በሰው ሃይል ያልተሟሉ መደቦች በጀት እንዲፈቀድላቸው ድጋፍ ያደርጋል፤

ሠ) በየዞኖች የተፈጠሩ ቅሬታዎች ካሉ በየደረጃቸው መፈታታቸውን ያረጋግጣል፤

ረ) ለዞን ሲቪል ስርቪስ መምሪያ እና ጤና መምሪያዎች በመመሪያው ላይ ግልጽነት ይፈጥራል፤

መ) ዝውውር ከመሰራቱ በፊት ለባለሙያዎቹ የዝውውር ፎርማቶቹ ደርሰዋቸው ግልጽነት ኖሯቸው መሙላት እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ስራ መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

2/ የዞን ሲቪል ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በመንግስት ድጋፍ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመጡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ወደ መጡበት ወረዳ ምደባ ይሰጣል፤

ለ) በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የዝዉዉር ፎርሙን በወቅቱ ተሞልቶ እንዲመጣ ለሁሉም ወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ያደርጋል ስለመድረሱም ያረጋግጣል፤

ሐ) በዞኑ እና በስሩ ባሉ ወረዳዎች የሚሰሩ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝዉዉር ፎርም በወቅቱ ተሞልቶ እንዲላክለት በማድረግ እና ትክክለኛነቱን

በማረጋገጥ ዝዉዉሩን ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ችግሮች ካጋጠሙም ከዞኑ ጤና መምሪያ ጋር በመተባበር መፍትሄ ያፈላልጋል፤

ሐ) በተቀመጠው የማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት በመደበኛ ዝውውር ጊዜ ወደ ሌላ ዞን የሙሉትን ባለሙያዎች ዝርዝር በመያዝ ቦታ መኖሩንና እንደሚቀበሉ መረጃ ይለዋወጣል፤

መ) በተቀመጠው የማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት በመደበኛ ዝውውር ጊዜ ከዞን ወደ ዞን የተዛወሩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ለተወዳዳሪዎች ውጤቱን ይፋ ያደርጋል።

3/ የወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በወረዳው ተመልምለው የስለጠኑናትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመጡ የጤና/ ኤክስራተኞችን ከጤና ጽ/ቤት ጋር በመሆን ምደባ ይሰጣል፤

ለ) የወረዳው ሰቪልሰርቪስ ጽ/ቤት በሚመለከተው ኦፊሰር አማካኝነት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች የዝውውር መረጃ አሰባስቦና አጠናቅሮ ምዝገባ ካለቀበት ቀን ጀምሮ በ7 ቀናት ውስጥ ውጤቱ ግልፅ በሆነ ቦታ እንዲለጠፍና በክላስተር ጤና ጣቢያቸው አማካኝነት እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፤

ሐ) በመረጃ መዛባት ቅሬታ የደረሰው የወረዳው ሰቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ቅሬታውን በአግባቡ ተመልክቶና የቀረበውን የዝውውር መጠየቂያ ፎርም በማገናዘብ ያለቀለትን ዝርዝር የዝውውር ውጤት ከዝርዝር መግለጫ ጋር በ5 የስራ ቀናት ውስጥ አጠናቆ ውጤቱን ግልፅ በሆነ ቦታ ይለጥፋል፤

መ) የሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤቱ የዝውውር ውጤት በ5 ስራ ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዳቸው የክላስተር ጤና ጣቢያዎች በደብዳቤ እንዲደርስ ማድረግ ይኖርበታል።

4/ ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የመደበኛ ዝዉዉር በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ ተግባራዊ እንዲሆን የውድድር መስፈርቱን መሰረት በማድረግ ለዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት መምሪያ ቴክኒካል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል። ችግሮች ሲያጋጥሙም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

ለ) በዞኑ የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የተሰራውን ስምሪት ይከታተላል።

ሐ) ከዞን የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ የሚፈለግ መረጃ ሲኖር መረጃውን ለጤና ጥበቃ ቢሮ ያስተላልፋል፤

መ) የዞንና ለዞን ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ማለትም የወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የሰው ሃይል ስምሪት ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፤ ችግሮች ሲያጋጥሙ የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳል።

ሠ) ለዞንና ለተጠሪ ተቋማት የሚያስፈልገውን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ እቅድ ያዘጋጃል፤ የተፈቀዱ መደቦች በሰው ሃይል መሟላታቸውን ይከታተላል፤ በሰው ሃይል ያልተሟሉ መደቦች በጀት እንዲፈቀድላቸው ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ) በዞን ውስጥ የሚፈጸመውን የጤና ኤክስቴንሽን ስምሪት በመመሪያው መሰረት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መተግበሩን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

ሰ) ስራውን የሚከታተል ባለሙያ (focal person) ይመድባል።

5/ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) መደበኛ ዝውውሩ በተቀመጠዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲፈፀም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል። የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ቴክኒካል ችግሮች ሲያጋጥምው አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

ለ) በወረዳው የሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የተሰራውን ስምሪት ይከታተላል።የተደራጀ የሰው ሃብት መረጃ በወረዳው ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል፤

ሐ) ለወረዳው ተጠሪ ተቋማት የሚፈጸሙ የሰው ኃይል ስምሪት ይከታተል ፤ይቆጣጠራል፤

መ) ከሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት ጋር አብሮ የሚሰራ አንድ ሰራተኛ ይወክላል፤

ሠ) የዝውውር ደብዳቤ የደረሳቸው ሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች ደብዳቤው በደረሳቸው በ 15 የስራ ቀናት ውስጥ በጃቸው ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን ወይም የተሰሩ ስራዎችን፣ፋይሎችና ንብረቶችን አዲስ ለተመደበች/ለቀረች የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ/ባለሙያ ርክክብ በመፈፀም አዲስ ወደ ተመደበችበት ቀበሌ ወይም በመሄድ ስራ እንድትጀምር ክትትል ያደርጋል፤

ረ) በሲቪል ሰርቪስ ተሰርቶ የሚቀርብለትን ዝውውር የጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊው ወይም ምክትል ኃላፊው ዝውውሩን ያጸድቃል።

6/ *የክላስተር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ተግባርና ሃላፊነት*

ሀ) በጤና ጣቢያው የሚሰሩ ጤና ኤክስ/ባለሙያዎች የዝውውር ፎርም በጥንቃቄ በማስሞላት በተወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በወቅቱ ለወረዳ ሰው ሃብት ልማትና ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፤

ለ) ለጤና ጣቢያው የሚያስፈልገዉን የጤና ኤክ/ ሰራተኛ በመጠንና በቀበሌ በመለየት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፤

ሐ) የጤና ጣቢያውን የጤና ኤክ/ሰራተኛ መረጃ በአግባቡ በማደራጀት መረጃ ሲፈለግ ለወረዳ ጤና ጥበቃእና ለሰው ሃብትልማትና ሲቨል ሰርቪስ ጽ/ቤት ያቀርባል፤

መ) የክላስተር ጤና ጣቢያው ከሲሰቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት የደረሰውን ዝውውር ደብዳቤ በሶስት የስራ ቀናተ ውስጥ ለጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ማሳወቅ፤

ረ) የክላስተር ጤና ጣቢያ ኃላፊ ወይም ተወካይ የሚዛወሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች የዝውውር ደብዳቤ እንደደረሳቸው የንብረት እና መረጃ ርክክብ በአግባቡ መፈፀሙን እና በክላስተር ቀበሌዎች ስራ መጀመራቸውን በአካል ተገኝተው ማረጋገጥ አለባቸው።

7/ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የዝውውር ዝርዝር መረጃ የደረሳቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች ዝርዝሩን አይተው የመረጃ ስህተት ያለበት ከሆነ በ5 ቀናት ውስጥ በማመልከቻ ቅሬታቸውን ለሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ማቅረብ፤

ለ) በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 7 በፊደል ተራ (ሀ) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ ማወቅ፤

መ) የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር ደብዳቤ ከደረሳት በኋላ ዝውውሩን መሰረዝ እንደማይቻል ማወቅ።

## 11. <u>የዝውውር ወቅትና አፈጻጸም</u>

1/ በወረዳ ደረጃ የዝውውር ፎርም የሚሞላበት ጊዜ ሐምሌ 1 እስከ ሃምሌ 30 ቀን ይሆናል፤

2/ በወረዳ ደረጃ ዝውውር የሚሠራበት ጊዜ ከመስከረም 1 እስከ መስከረም 30 ቀን ይሆናል፤

3/ አንዲት ዝውውር ጠያቂ ዝውውር ተሰርቶ ከማለቁ በፊት የዝውውር ጥያቄዋን ከመስከረም 1 በፊት መሰረዝ ትችላለች፤

4/ አንድ ጊዜ ተሞልቶ የቀረበ የዝውውር ጥያቄ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ/ለአንድ የበጀት አመት ብቻ ነው።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 12. <u>ልዩ ሁኔታ</u>

1/ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ሌሎች የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ተግባራት በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

2/ ማንኛውም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ህጋዊ ባልሆነ /በተጭበረበረ /ሐሰት/ ማስረጃ ጋብቻ እንደፈጸመች በማድረግ ወይም የህክምና ማስረጃ ወይም በሌላ ምክንያት ዝውውር እንዲታይላት ወይም እንድትዛወር ያደረገች ወይም ያቀረበች መሆኑ ሲረጋገጥ በዲሲፒሊን ስነ-ስርአት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ትጠየቃለች። ወደ ነበረችበት ቀበሌም ትመለሳለች፤

3/ ማስረጃ ሳይቀርብ እንደቀረበ አድርጎ ዝውውር የፈፀመ ወይም ያስፈፀመ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ በዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ መሰረት ይጠይቃል፤

4/ ይህን የስምሪት መመሪያ በተዛባ መልኩ ወይም ያለአግባብ የሚፈፀም /የሚያስፈጽም/ አካል ወይም የስራ ኃላፊ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፤

5/ አላግባብ ተሞልቶ በተላከ መረጃ ለሚፈጠረው ችግር መረጃውን አላግባብ የሞላ ባለሙያ/ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፤

6/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያው በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማጥናት መመሪያው ሊሻሻል ይችላል፤

7/ ማንኛውም በዝውውሩ ቅሬታ ያለውና አድልኦ ተፈጽሞብኛል የሚል የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያ መደበኛውን የቅሬታ ስርዓት ተከትሎ በየደረጃው ቅሬታዋን/ቸውን ማቅረብ ይችላል።

## 13. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

2/ ከዚህ ቀደም ጤና ጥበቃ ቢሮ ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር በ2002 ዓ.ም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የዝውውር፣ የመልቀቂያና ልዩ ልዩ የዕረፍት ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአብክመ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 15. መመሪያው ስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ከፀደቀበት ከጥር 01/2011 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደጠጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በፍትሕ ቢሮ ከተመዘገበበትና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኃላ ተፈጻሚነት የሚኖረው በአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡